

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

አንደኛ ዓመት ቁጥር 2
ሠመራ-ሚያዝያ 4 ቀን 1990 ዓ/ም

በአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ምክር-ቤት ጠባቂነት የወጣ

1th year No. 2
SEMERA- 12th,Aprile 1998

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪/፲፱፻፺ ዓ.ም

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ .....ገጽ 1

አዋጅቁጥር ፪/ ፲፱፻፺ ዓ.ም

የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ

ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በህግ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባራት ለመወጣት የሚያስችሉ የራሱ ህጎች በክልሉ ም/ቤት ተመክረው የወጡና የሚወጡ በመሆኑ፤

በክልሉ ም/ቤት የወጡ የተለያዩ ህጎች ኃይል ኖሯቸው ተፈፃሚ የሚሆኑት የህጉ ተጠቃሚ የሆነው ህዝብና የክልሉ መስተዳድር የህግ አውጪ፣ የህግ ተርጓሚና አስፈፃሚ አካላት በህዝብ ጋዜጣ በቅድሚያ እንዲያውቁት ሲደረግ ስለሆነ ህጎች የሚወጡበት ኦፊሴል ጋዜጣ ማቋቋም በማስፈለጉ ፣

በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፯ በንዑስ አንቀጽ ፫/ሀ/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

<u>አንቀጽ ፩</u>

<u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ «የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

<u>አንቀጽ ፪</u>

<u>መቋቋም</u>

በዚህ አዋጅ የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ ተብሎ የሚጠራ የክልሉ መስተዳድር ጋዜጣ ተቋቁሟል።

<u>አንቀጽ ፫</u>

<u>በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ የሚወጡ ጉዳዮች</u>

፩.የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ የሚወጡ ጉዳች ለክልሉ መስተዳድር የተለያዩ አካላት በክልሉ ሕገ መንግስት በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት

ሀ) የክልሉን ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮች

ለ) ከፍተኛ የክልሉ ባለስልጣኖችን ሹመት፣ ሽረት፣ የማዕረግ ስም ሽልማትና ኒሻን፡

ሐ) ለህዝብ ጥቅም ያላቸው የክልሉ ህዝብ ማወቅ የሚገባቸው ማስታወቂያዎች ናቸው።

፪.በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ የሚወጡ ህጎችም በክልሉ ሕገ መንግስት ደንብ ለማውጣት ሥልጣን ባላቸው አካላት ከዚህም በላይ የተገለፁትን ጉዳዮች ለህዝብ ለማስታወቅ የሚወጡ አዋጆች፣ድንጋጌዎች፣ደንቦችና የህግ ክፍል ማስታወቂያዎች ይሆናሉ።

<u>አንቀጽ ፬</u>

፫. <u>በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ ህጎችን የማውጣት ስልጣን ያላቸው አካላት ፡</u>

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ ህጎችን ደንቦችን፡አዋጆች ድንጋጌዎችን የህግ ክፍል ማስታወቂያዎች ማውጣት የሚችሉት ከዚህ በታች የተመለከቱት ናቸው።

ሀ) የክልሉ ምክር ቤት

ለ) የክልሉ ምክር ቤት ስልጣን ሲሰጠው የክልሉ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ናቸው።

፬. <u>የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ ነጋሪት ጋዜጣ ቅርፅ/ፎርም/</u>

ሕጋዊ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚሠራ የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ የሚከተለው /ቅርፅ/ ፎርም የሚያሟላ ነው።

፭. የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ነጋሪት ጋዜጣው ተከታታይ ቁጥሮችን በመያዝ የክልሉን መስተዳድር አርማ ያለው ሆኖ የማዕከላዊ መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ ቅርፅ/ፎርም/ ይኖረዋል።

፮. በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ነጋሪት ጋዜጣው ግርጌ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ማህተም ያረፈበት መሆን አለበት።

<u>አንቀጽ ፯</u>

፯. <u>የህጎች ተፈፃሚነት</u> ፡

በዚህም አዋጅ በተቋቋማ በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ የሚወጡ አዋጆች ድንጋጌዎች ደንቦችና ሌሎች የህግ ክፍል ማስታወቂያዎች በማነኛውም የክልሉ መስተዳድር አካላት ተፈፃሚ ይሆናሉ።

<u>አንቀጽ ፯</u>

፯.አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ፤

ይህ አዋጅ በዚህ መሰረት በተቋቋመ በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።